# *ማን ያውቅ አገር - ማን ያጥብቅ ማገር!*

*ከሀገር ወዳዶች*

*መሪነት በአምሮት ሳይሆን፤ ራስን በመሾም ሳይሆን፤ በህዝብ የሚሰጥ ያደራ ቃል ነው። በአመኔታ የሚፈቀድ በተግባር የሚፈተን የስራ ምድብ ነው። ግልፅነትን የሚያውቅ፤ ሰብአዊነትን የተላበሰ፤ ከሃዲነትን የሚፀየፍ፤ ለህዝብ ታዛዥ የሆነ፤ ቀራጥ መሪ ጋር መንዝ ምንኛ የመንፈስ ዕርካታ ይሰጣል። ይህን መሰል ጀግና በመሪነት የያዘ፤ ለተከበረ ታሪካዊ ስራ፤ ለታሪካዊ ሞት ይታደላል እንጂ! አልባሌ ሞት እንዲሞት፤ በሀፍረት እንዲሸማቀቅ አይሆንም። ህዝብ መብቱን እንዲያውቅ በየገጠሩ ዞር፤ በየታዛው አድሮ፤ ያደራጀ መሪ። ህዝብ መብቱን እንዳያስነካ የሚያበረታታ ግምባር ቀደም መሪ፤ ሀገርን ለመታደግ ህዝብን እስተባብሮ የገጠርና የከተማው ነዋሪ ባንድ ስሜት ላንድ ዐላማ እንዲቆም የሚያስደርግ መሪ። የህዝብን ስሜት የሚጋራና በተግባር የሚያውል መሪ፤ ህዝብ የሚፈልገው ይህን አይነቱን መሪ ነው። ለዚህ ቦታ ለመታጨት ደግሞ ሆኖ መገኘትን የግድ ይላል። የህዝብ የምስክርነት ቃል ሀያል ነው። ኢንጂኔር ሀይሉ ሻውል የዚህ ሁሉ ባለፀጋ ለመሆናቸው የህዝቡን ድምፅ መስማት ያስፈልጋል።*

*የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን! ምሁራኖቻችን ለምን ዓላማ ብለው የህዘቡን ድምፅ ወደ ሁዋላ በማድረግ ሊያወናብዱ እንደሚሞክሩ አይገባንም። ይህ በምሁራኑ ከውጭም ከግቢም የሚካሄደው የተቀናጀ አድማ በቀጥታ በሀገር በወገንና በራስ ላይ የተቃጣ አደጋ መሆኑን ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲረዳው ያስፈልጋል። በሀገር ውስጥ በአድማ ላይ የሚገኘው የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት አፈንጋጭ ቡድን፤ ትግሉ በከፍተኛ ደረጃ ኢንጂኔር ሀይሉን በማስወገድ ላይ ያነጣጠረ መሆኑ እየተገለጠ ነው። ከድርጅቱ ውስጥ 5 የሚደርሱ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት በፓርቲው ፕሬዚዳንት ጊዜያዊ ዕገዳ የተጣለባቸው መሆኑን በመቃወም ድጋፋቸውን የሰጡ ወገኖችም እንዳሉ በድህረገፆች ላይ ወጥተው ተመልክተናል። እንደ ድህረ ገፁ ከሆነ እነዚህ ወገኖቻችን የሚከተሉት ናቸው።*

1. *ዶር. ያዕቆብ ሀይለማርም - ከአውሮጳው ልዑክ ጋር የነበሩ፤ ባሁኑጊዜ በዕረፍት ላይ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በአሜሪካ የሚገኙ*
2. *ዶር. ብርሃኑ ነጋ - አወጣጣቸው ግራ የሚያጋባ/ በሰራ ዕድል ምክንያት በአሜሪካ የሚገኙ*
3. *አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ - ነዋሪነታቸው በእንግሊዝ አገር የሆነ*
4. *ዶር አድማሱ ገበየሁ - በጥገኝነት ጥያቄ ላይ ስዊድን የሚገኙ*
5. *ዶር. መሉዓለም ታረቀኝ - በጥገኝነት ጥያቄ ላይ ስዊድን የሚገኙ*
6. *አቶ ቸኮል ጌታሁን - በጥገኝነት ጥያቄ ላይ ስዊድን የሚገኙ*
7. *አቶ ደበበ እሸቱ - ቁርጡ ያልታወቀለት የአሜሪካ ጉዞ ላይ ያሉ*
8. *አቶ አክሉ ግርግሬ - አገርም እወጭም የሚመላለሱ*
9. *አቶ አስቻለው ከተማ - አገር ገብተዋል የሚባል/አድራሻቸው በግልፅ የማይታወቅ*
10. *አቶ ዳንኤል አሰፋ - አሜሪካ በጥገኝነት ላይ ያሉ*
11. *መስፍን አማን - በሆላንድ በጥገኝነት ላይ ያሉ*

*ሁሉም ከሀገር ርቀው የሚገኙ ስለሆነ በፓርቲው ጉዳይ ላይ ጣልቃ ሊያስገባ የሚያስችል መብት የሌላቸው መሆኑ ይጠፋቸዋል ብለን አንገምትም። ሆኖም ግን ቁጥር ለማብዛት ብለው ያደረጉት ድጋፍ መሆኑን እንገነዘባለን። ለነገሩማ!*

*የተማሪ ወዳጅ ቢቀር ምናባቱ፤*
*ጎራዴ ሲመዘዝ ይላል ባዛኝቱ። ይባል የነበረውን የአባቶች ትዝብት ለመሻር ይመስላል።*

በጉልበት በር ሰብሮ፤ አጥር ነቅንቆ ለመግባት በተወሰደው እርምጃ የተማረው ክፍል ጀግንነቱን አስመስክሯልና ቪቫ! ዶር. በፍቃዱ ደግፌ! ፤ ቪቫ! ዶር. ሀይሉ አርአያ የሚል ድጋፍ የሰጡት። ምንም እንኳ! በዚህ ዕድሜ ያለ ህመም ቆሞ መሄድ በራሱ መታደል ቢሆንም ለቡጢ መሰለፋቸው ደግሞ ምሁራኖቻችንን ብራቮ የሚያሰኛቸው ሆኖ በደጋፊዎቻቸው ብራቮ እየተባሉበት ነው። የሚያስገርመው ግን ይህን አይነቱን ህግ አልባነት የዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ እንዲደግፍ ጥሪ መደረጉ ነው። አዲስ አበባ ያሉት አዛውንት ምሁራኖቻችን በበር ሰበራው ላይ ግምባር ቀደም ሚና መጫወታቸው በፍፁም ህጋዊም ምክንያታዊም አይደል። ህጋዊነቱ ለህግ ጣሽ ሊሰራ ባይችልም፤ ምክንያታዊ ላለመሆኑ ግን የዘማቾቹን ዕድሜና ዐቅም፤ የተነሱበትን ዓላማ መመልከቱ በቂ ይመስለናል። የድርጅቱን ፕሬዚዳንት ውሳኔ አንቀበልም የሚል አባል ያንንም በዐመፅ እንቀለብሳለን የሚል አባል፤ ለመሆኑ ስለየትኛው ዲሞክራሲያዊ አሰራር ነው ሊነግረን የሚፈልገው? ለማንኛውም! ሶስተኛው ዙር መቼ እንደሚሆን ባይታወቅም፤ የታገዱት የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ዳግማዊውን ዘበኛ ገፍትሮ የመግባት ሙከራቸውን ባለፈው ሳምንት ማከናወናቸው ታውቋል።

<u>የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን!</u>

መከራውን እያየ የሚኖረውን ህዝብ እንወክላለን ለማለት የሚዳዳቸው በአውሮጳና በአሜሪካ በጥገኝነት ጥያቄ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች፤ የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት ወይም የጠቅላላው ምክር ቤት አባል ነን በሚል ሰውን ማዋዛቱን ማቆም ይገባቸዋል። ይህ የብዙ ወገኖቻችንን ህይወትና የኑሮ መፋለስ ያስከተለ ጉዳይ በዝምታ የሚስተዋል ሊሆን አይችልም። በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ማንም ለማንም አስተማሪና መካሪ ሆኖ ሊቆም አይችልም። እንደ እውነቱ ከሆነ እያንዳንዱ ተማርኩ ያለ ወገን ለዚህ ለደረሰበት ደረጃ የኢትዮጵያ ደሃ ገበሬ ላብ አለበት። የፈረንጆቹ እጅ ቢገባበት እንኳ! ከባለቀ በሁዋላ ያገኛቸው በመሆኑ፤ ለዚህ ያበቃውን ህዝብ፤ በችግር የሚገኘውን ህዝብ፤ ለማጥቃት መሞከር በነፍስም በስጋም ያስጠይቃል። ህዝቡ በሀገሩ ላይ መኖር አቅቶት እየተንገላታ ነው። ወጣቶች በየክፍለ አለማቱ የስደተኝነት መብታቸው እየተጣሰ ነው ያለው። በየመንገዱ በየስርቻው ተሸማቀው እንዲኖሩ እየተገደዱ ነው ያሉት። በየጎረቤት ሀገራቱ ሳይቀር ወገኖቻችን እየተገደሉ ነው። ለወንድሞቻችን፤ ለእህቶቻችን፤ ለልጆቻችን በየሀገሩ ለሚንገላቱ የስደተኞች መብት መከበር ተባብረን እንዳንነሳ፤ አብረን እንዳንቆም፤ በችግራችን እንዳንረዳዳ፤ እንዳንከባበር፤ የተለያየ ሴራ በየጊዜው እየፈበረኩ ሊለያዩን ሲጥሩ ከማየት በላይ ምን አሳፋሪ ድርጊት አለ። ዛሬ ህዝባችን የሚደርስበት እያጣ ነው። ከፍተኛ ችግር እያጠቃው ነው። ታዲያ በማ! ላይ ነው ቀልዱ? ስንቶቹ ችግረኛ ስደተኞች ናቸው እንደ እነ ዶር. ብርሃኑ ከተጎዘጎዘ ቀጤማ ላይ ያረፉት? ስንቶቹ ስደተኞች ናቸው ዛሬ በስደት አለም እንደ ላዕላይ ምክር ቤት አባላቱ እንኳን ደህና መጣችሁ ተብለው የሞቀ ቤት የጠበቃቸው? የላዕላይ ምክር ቤት አባልነት ካርድ የራስን የስደት ህይወት ከማመቻቸት በላይ ለህዝቡ ምን የፈየደው ነገር አለ? እነዚህ ናቸው በውጭው ዓለም ስለኢትዮጵያዊው መናገር የሚችሉ? እነዚህ ናቸው በኢንጂኔር ሃይሉ ላይ ዱለታ የሚያኪያሂዱ፤ የሚንቁና የሚያዋርዱ? ዓላማቸው ምን እንደሆነ ግልፅ ነው። ፍርዱን የዚያ የድሃ ህዝብ አምላክ ይስጥ! ጥንትም ቢሆን!

ኢትዮጵያ ሀገሬ - ሞኝ ነሽ ተላላ፤
የሞተልሽ ቀርቶ - የገደለሽ በላ! ተብሏል። በእርግጥም ነው።

ገዥም ሀይሉን አጠናክሮ አፍኖ ለመግዛት ቢጥር! አሸርጋጅም በምቾት ዓለሙ ውስጥ ተወሽቆ በድሃ ህዝብ ስም ለማጭበርበርና እጅ መንሻ ለማድረግ ቢሞክር! ኢትዮጵያዊ በሀገሩ ጉዳይ በእሳት የተፈተነ የጠራ ወርቅ ነው። በሃብት ይደህይ እንጂ! የተመክሮ ባለፀጋ ነው። የባህል

ሁብታም ነው። የመከራ ኑሮው ቢጨምር፤ ስቃዩ ቢበረታ! ለጠላቱ እጅ ሰጥቶ አያውቅም። በሀገሩ በሰንደቅ ዓላማው ተደራድሮ አያውቅም። እየተሰቃየና እየሞተ የሚቀጥልበት ዘመንም ያበቃል። የቴሌቪዥንና የራዲዮ ኢንተርቪው አንበሶች፤ የህዝብ ልጅ ለሀቁ ሲዋደቅ እነሱ ካጠገቡ በመራቅ ወገናዊነታቸውን አሳይተውታል። በስመ ትምህርት አሳቦ ሲያመች የኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ መፈናጠጥ፤ ሳያመች ደግሞ ጓዝን ሸክፎ መፈርጠጥ፤ ከሆነ ድሮም ቢሆን ከፖለቲካው ውስጥ ጥልቅ ማለት አይገባም ነበር። ትግል ዲስኩር እንደማሳመር አይቀናም። ሁልጊዜም ተደብቆ መዝለቅ አይቻልምና። በኢትዮጵያ ህዝብ ስም የሚቀልዱ ሁሉ ይጋለጣሉ!!

የኢትዮጵያ ልጆች! ወገን፤ ሀገር፤ ዘመድ፤ ሲሉ ትርጉማቸው ሁሉ መሰረት የሚያደርገው በሃቅ፤ በክብርና በመፈቃቀር ላይ እንጂ የተፈጥሮ ግንኙነቱን ጫና ሰጥተው፤ ሌባ ወንድምን፤ ገዳይ ዘመድን፤ አቅፈውና ደግፈው ሸፍነው ይኖራሉ ማለት አይደለም። ዘመድ ወንድም እህት መገለጫው የሀገር ክብርና ደህንነት በመሆኑ፤ ወንድም ወንድሙን ቢያዋርደው፤ ግንኙነቱን ስጋነቱን ጠልቶና ንቆ አይደለም። የሀገሩን ታሪክና የወገኑን ክብር አላስነካም ብሎ የሚሸፍት ሁሉ፤ ከበዳዩ ክፍል ጋር በደም በስጋ መገናኘቱን ዋጋ ሳይሰጠው ቀርቶ ሳይሆን፤ ለእውነትና ለሀቅ መቆምን በመምረጡ ነው። በዚህም ሁኔታ በርካታ ዝምድና ተሸረዋል። ብዙ ቤቶችም ፈርሰዋል። መሰረቱ ግን ሀቅ ነው። ኢትዮጵያዊነት ፍልስፍና ነው፤ ኢትዮጵያዊነትን መጠበቅ ማለት በሰው ልጆች መሃል ፍቅርን መቻቻልን ማንገስ፤ መከባበርን፤ አብሮ መኖርን፤ ተሰባጥሮ መፈጠርን፤ ዕኩልነትን መቀበልና፤ በነፃነት ማመንን፤ ከፍ አድርጎ መያዝ ነው።

ስለዚህም ኢትዮጵያን እንወዳታለን እናፈቅራታለን ሲባል፤ የጥቁር ህዝብን እኩልነት ማወጃ መድረክ መሆኗን መመስከራችን ነው። ለሃይማኖቶች ሁሉ ተቻችሎ የመኖር ካስማ የተተከለባት የመሰረት ስፍራ ናታና ኢትዮጵያን እናከብራታለን ማለት ነው። ኢትዮጵያን እንወዳታለን ስንል፤ ጠይሙ፤ ጥቁሩ፤ ቀዩ፤ ጨዋው፤ ደጉ፤ የዋሁ፤ ሩህርሁ፤ በተፈጥሮ አዋቂው፤ ምሁሩ፤ በርከትከት ብሎ የተፈጠረባት ምድር ናትና በቀላሉ አትጠቃም ማለታችን ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ላይ አንገታችንን ቀና አድርገን የምንታይ ህዝቦች እንጂ የማንም አጎባዳጅ አለመሆናችን መታወቅ አለበት። ዜጎቿ በየዘመናቱ የሚከሰቱ ጠላቶቿን ተናንቀው ለክብሯ የሚዋደቁት በዚሁ አትንኩን ባይነት ስሜት ነው። ህዝቧ ነፃነቱን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ የዜግነት ግዳጁ መሆኑን የተረዳ ነው። ኢትዮጵያ ከዜጎቿ ሌላ ለነፃነትዋ የውጭ ዕርዳታ ጠይቃም አታውቅ። ጠላቶቿን ተቋቁማ የኖረችው በራሷ ነው። ሌላው እንዲታገልላት፤ ሌላው እንዲጠብቃት ፈቅዳም አታውቅ ወደፊትም አትፈቅድ። ኢትዮጵያ ከእውነተኛ ልጆቿ በቀር ረዳት የሌላት ብቸኛ ሀገር ብትሆንም ረዳቷ ጠባቂዋ አምላኳ ብቻ ነው። አጭበርባሪዎች በኢትዮጵያ ስም ሊነግዱ ቢፈልጉ፤ ሊያጠፏት ቢያሴሩ ስሟን ከመፅሃፍ ቅዱስና ከቁራን ውስጥ ያስከተበች ቅድስት ሀገር ነችና በፍፁም አይቻላቸውም። ምንም እንኳ ልቡናቸውን ባጡ ልጆቿ አጋላጭነት በዘመናችን በደረሰባት መከራና የህዝቧ ስቃይ ብትጎሳቀልም፤ ኢትዮጵያ አትሞትም። ከታሪክም አትፋቅም። ኢትዮጵያዊ ሆይ! ለሀገርህ ለክብርህ ለወገንህ ለራስህ ማንነት ቁም! የበግ ለምድ በለበሱ ተኮላዎች መሞኘትህን አቁም! እጅ ለእጅ በመያያዝ ፍቅርህን አደርጅተህ፤ ጎታቾችን ገለል አድርገህ፤ ይህን የታሪክ ወቅት በድል ለመወጣት ቆርጠህ ተነስ!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!